# ተዝካር ወይም መታሰቢያ

ቀሲስ አስተርአየ ጽጌ
nigatuasteraye@yahoo.com

ጥቅምት ፳፱ ቀን ፳፻፫ ዓ.ም.

"ብኪ ወልድየ ላዕለ ዘሞተ፥ ወላህዎ ወአሕምም ርእሰከ:: ወበከመ ግዕዙ ግበር ሎቱ ተዝካሮ:: ወኢተጸመም ሞቶ ለዘተልአከከ"(ሲራክ ፴፰:፲፮):: ማለት:-

"ልጄ ሆይ! ለሞተ ሰው አልቅስ፡ እዘንለት፥ ራስህንም አሳዝን፥ ይልቁንም ላንተ ቆሞ ላንተ ተጋርዶ ለሞተልህ ወገን አዘንህ የመረረ ይሁን:: በባሕሉም ተዝካር (መታሰቢያ) አድርግለት" ሲራክ የተባለው መካሪ በሕይወት ያለ ለሞተ ወገኑ እንዲያለቅስ፥ ምርር ብሎም እንዲያዝንና ተዝካር ማውጣትም እንዳይተው ይመክራል:: "ይልቁንም ህዝባዊ በሆነ ጉዳይ እራሱን አሳልፎ ለሞት ለሰጠ ወገን የበለጠ ከማድረግ ቸል አትበል" እያለ የተዛካሩን ያፈጻጸም ሥርአት አወዳድሮ በማበላለጥ ይህ የተፈጥሮ ግዴታ እንዲደረግ ለቆመ ሰው አጥብቆ ያሳስባል:: ተዝካር (መታሰቢያ) ከዚህ ዓለም ለተለየ ወገን ሲደረግ የኖረና የተለመደ ባህላችን ነው:: ቆመው በሚሄዱ ወገኖች ሕሊና እንደ እርም ከሚቆጠርባቸው ነገሮች አንዱ፥ ለሞቱ ወገኖች ተዝካር (መታሰቢያ) አለማድረግ ነው:: እንስሳትም የወገናቸው ደም በፈሰሰበት ምድር ላይ የሚአደርጉት ጩኸት በተፈጥሮ ቋንቋቸው ተዝካር ከማውጣት የተለየ እንዳልሆነ መገመት ይቻላል:: ጥልቅ የተፈጥሮ ምሥጢርና ግዴታ መሆኑንም ያስረዳል::

ጥበበኛው ሲራክ በጠበቀ አደራ ለቆመ ያስገነዘበውን ይህን የተፈጥሮ ሕግ መሠረት በማድረግ፥ አባቶቻችን በተፈጥሮ ግዴታ ለሞቱት እህል ውሐ ይዘው ወደጀ ሰላም በመሄድ መታሰቢያ ያደርጋሉ:: "ያገለገለህን ሰው ሞት ችላ አትበል" በተባለው መሠረትም፥ ሳይታመሙ እርጅና ሳይጫናቸው ለአገር ለወገን ሲሉ የወጣትነት ሕይወታቸውን ለሰውት ኢትዮጵውያን አራት ኪሎ ላይ ሐውልት ሠርተዋል:: "ወንጌል መስበክ ብቻ አይደለም፥ ነፍሳችንን ለማካፈል በጎ ፈቃዳችን ነበር:: ለኛ የተወዳችሁ ሆናችሁ ነበርና"(፩ኛ ተሰ ፪:፰) እንዳለው ቅዱስ መጽሐፍ፥ ምንም እንኳ ለወገን ተጋርዶ መሞት ክህነቱ ቢአስገድዳቸውም፥ ውለታ የማይረሳው ሕዝባችን ገዳም ሰፈር ላይ በብሔራዊ ጉዳይ ለተረሸኑት ለአባታችን ለአቡነ ጴጥሮስ ከሞቱ በኋላ ሐውልት ሰራላቸው:: ቤተክርስቲያናችንም በደብረሊባኖስ ገዳም ያቋቋሙት ያንድምታ ትምህርት ቤት በጣሊያን እጅ የሞቱትን የሊቁን የመምህር ገብረ ኢየሱስን ውለታ ለማስተወስ ነበር::

የጥበበኛውን ምክር ያጤኑ መንፈሳውያን አባቶች "አኀውየ ፍቁራንየ ብቁኡኒ በሕገ ፈላሲ፥ ወከመ ሐላፊ ህልው፥ ወአርሕቅዋ ለፍተወተ ሥጋክሙ እንተ ትጸብአ ለነፍስክሙ" (መዋሲት ዘፈላስያን):: ማለትም "የተወደዳችሁ ወገኖቼ ሆይ! እንደሚችና አልፎ እንደሚሄድ ሰው አስቡ:: ነፍሳችሁን፥ ሞራላችሁን የምትዋጋውን ከንቱና አላፊ ነገርን ከሕሊናችሁ አርቁ" እያሉ ሞቶ በተጋደመ ሬሳ ዙሪያ የቆመ ወገን ሊሰማው በሚችለው ከፍ ባለ ድምጽ፥ በሐዘን፥ በትካዜ ያንጎራጉራሉ:: ይህ አባባል የሚያመለክተው ጥቅም፥ ሹመት፥ ገንዘብ ለማግኘት ሲሉ በግፍ የሞቱትን ረስተው ከገዳዮች ጥቅም የሚፈልጉትን ጠልሰመኞች ለመገሰጽ ነው::

ሰው የጸሐይ ጨረር ሲሸሽው ጠፍቶ የሚቀር ጥላ መሆን የለበትም:: ከመብላት፥ ከመጠጣትና ከመራባት ባሻገር፥ ሲሆን አዳብሮ፥ ካልሆነ የነበረውን ሳያጎድል ጠብቆ ለቀሪው ትውልድ አውርሶት

የሚአልፈው መታሰቢያ ሊኖረው ይገባል:: ውርስ የሚባለው፥ በእሳት ተቃጥሎ አመድ የሚሆነውን የቤት አዳራሽ፥ ጊዜ ከፍና ዝቅ የሚያደርገውንና፥ ጨርሶም የሚያከስረውን ብር፥ ወረርሽኝ በሽታ የሚአረግፈውን የእንስሳ ሐብት አይደለም:: ውርስ የሚባሉት ሰባዊ ልዕልና፥ አገር፥ ድንበር፥ ባሕል፥ ቋንቋንና ሃይማኖት፥ ታሪክን የመሳሰሉ ነገሮች ናቸው::

"የወደቀን አንሳ
የሞተን አትርሳ" እያሉ በግፈኞች የተገደሉትን እንዳንረሳ፥ የወደቁትንም እንዳንረሳ የሚያሳስብ ቅኔያቸውንም ወርሰናል::

ዛሬ የመታሰቢያ ጸሎተ ፍታት እንድናደርግ የቀረበልን ጥያቄ፥ በእኛችን ከጨበጥነው ቅዱስ መጽሐፍ የወጣ አይደለም:: ዮሐንስ በመልእክቱ "ሞት የሚገባው ኃጢአት አለ:: ስለዚያ እንዲጠይቅ አልልም:: ሞት የማይገባው ኃጢአት አለ" (፩ኛ ዮሐ ፭:፲፮-፲፯) እንዳለው፥ ተዝካር (መታሰቢያ) እንድናደርግ የተጠየቅነው፥ ነፍስ ገድለው ድንበር አፍርሰው፥ ሕግ ጥሰው፥ በትክለኛ ዳኛና ሕግ በኃጢአታቸው ተፈርዶባቸው፥ በሞታቸው እዳቸውን ለከፈሉ ወገኖች አይደለም:: ይህ መንግሥት አገር እያፈረሰ፥ ድንበር እየጣሰ፥ ባንዲራ እያቃጠለ ወደ ቤተ መንግሥት ከገባበት ሰአት ጀምሮ እስካሁን ድረስ ላለቁት ወገኖቻችን ነው:: ከነዚህ ሁሉ ጋር እኛም አብረን በስሜት በመንፈስ ሞተናል:: በምትሽከረከረዋ ምድር የሚጠነጠንብን ዘመን እያመጣ የሚአሽከመን የተደራረበ መከራ የፊተኛውን ቢሸፍነውም፥ ቀን ተወስኖ መታሰቢያ የሚደረገው በየጊዜው የሚፈጸመውን መከራ፥ በሩቅና ቅርብ ያለ ወገን በሰማንና ባየንበት ደቂቃ ሁሉ አላለቀሰም፥ አንጀቱ አላረረም ማለት አይደለም:: ደሙ ሲጠረግ ተዛካሩን ከሚረሱት እንስሳት የተለየን ሰዎች እንደሆንና ያባቶችን ባሕል ለመከተል የተደረገ ጥሪ መሆን አለበት::

ግማሽ ሕይወታችንን የምናሳልፈው እያሰብን በምንቀሳቀስባት ዓለም ላይ ምን እንደተፈጸመ መገንዘብ በማይችልበት በእንቅልፍ ላይ እያለን ከሞቱት ወገኖቻችን ጋር በመጫወት ነው:: ከእንቅልፋችን ስንነቃ በሕይወታችን አስቀምጠው ያለፉት ለተወሰነ ደቂቃ በትካዜ መንፈስ ወደተዝካር ይሻገራል:: በዚህ ሁኔታ ቁም ነገር እየሰሩ ያለፉ ወገኖቻችን እኛን ቆመን የምንሄደውን በሐውልታቸው፥ በሥራቸው ትዝታ (ተዛካር) ያጫውቱናል:: ይህንንም:-

"ያጫውታሉ የሞቱት፥
ቆመው ለሚሄዱት" ብለው አበቶች በበገናቸው ቃኝተውታል::



ጥልቅ በሆነ በመከራ ስሜት፥ በሰማይ ርቀትና በውቅያኖስ ጥልቀት ላይ ዓይኖቿን ተክላ ደረቷን እየደቃች በመረረ ሐዘንና ትካዜ፥ በስዕሏ የምናያት እህታችን ብርቱካን፥ ልትገልጸው ከቋንቋዋ በላይ የሆነውን በሷ ላይ የደረሰባትን ብቻ የሚአስታውሰን አይደለም:: በዚህ መንግሥት ልጆቻቸው

የተጨፈጨፈባቸውን፥ ባሎቻቸው የተገዱሉባቸውን እኅቶች፥ በጠቅላላው የመላ ኢትዮጵያውያንን ዋይታ፥ ሰቃው፥ ሐዘን፥ ብካይ እስከ ዓለም ፍጻሜ ድረስ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ሲያስታውሱበት የሚኖር ሐውልት ነው::እኛንም በአዕምሮዋ የሚወጣውንና የሚወርደውን ሐዘን ትካዜ በማሰብ አብረናት በመንፈስ እንድንጓዝ አድርጋናለች::

ሰው ሳይገሉ፥ ቋንጃ ሳይቆርጡ ለአገር: ለወገን: ለታሪካ ለሃይማኖት ሲሉ ለተገደሉ ሁሉ የማያዝን ካለ "በኃጢአታቸው ሞቱ" ከሚለን መንግሥት ጋራ ጥብቅ ግንኙነት ያለው የጠልሰም ደፍተራ ብቻ ነው:: የጠልሰም ደፍተራ መታሰቢያ (ተዝካር) ሲጠራ የሚታወሰው ሳንቲም የሚጠጣው ጠላ ነው:: ለጠልሰመኛ ደፍተራ ያ ከሌለበት የተዝካር ትርጉም የሳተ ነው:: እግዚአብሔር አሞጽ በሚባለው አማካይነት "ለዮሴፍ በመከራው ጊዜ አላዘናችሁምና የዳዊትን መሰንቆ የመዝሙር እቃዎችን ለምታዘጋጁ፥ በፋጋ የወይን ጠጅ ለምትጠጡ፥ እጅግ ያማረ ሽቱ ለምትቀቡ ስለ ዮሴፍ መከራ ለማታዝኑ ለእናንተ ወዮላችሁ!"(አሞጽ ፮:፬) ባለው ያካባቢያችንን ደፍተሮች የምንታዘብበት ወቅት ነው::

"በዚህ መንግሥት እጅ የሞቱት በኃጢአታቸው ነው" ብሎ እንደ አቡነ ጳውሎስ የሚያምን ሁሉ የሰባዊት ርኅራኄ የደረቀበት ደም የሌለው ሕዋስ ነው:: ወጣቶች፥ እናቶችና አዛውንቶች ያለቁት ሰውነታችንን አትግፈፉን፥ አትከፋፍሉን፥ አትለያዩን፥ አትዝረፉን፥ አትዋሹን አታታሉን አትግደሉን አታሰድዱን ንብረታችንን አትቀሙን ወዘተርፈ በማለታቸው ነው:: "በግፍ ሥራ ጸንተው የሚኖሩ ሰዎች ሁሉ ለዘላለም ይጠፋሉ:: በግፍ ሥራቸው ጸንታችሁ አትኑሩ እላችኋለሁ" (ሄኖክ ፲፬:፲፫) እንዳለው ይህንን እየተናገሩ ማለፍ በመጽሐፍ የተደገፈና እግዝአብሔር የሚቀበለው ነው::

ለእንዲህ አይነቱ ሰባዊ ጥያቄ፥ እኛ የሃይማኖት መሪዎች ቀዳሚዎች ሆነነ መገኘት ነበረብን:: ዛሬ በግፍ የተገደሉ ሰዎች በሚታሰቡበት ወቅት፥ ከፊት ተገኝተን አካላችንን ለመከራ ለማዘጋጀት ባንበቃ እንኳ በያለንበት ለሞቱት መታሰቢያ ጸሎት አለማድረግ ሥርየት የሌለው ክህደት ነው:: ጊዜውን ጠብቆ የተፈጥሮ ሞቱን ለሞተው ጠምጥምንና ካባችንን አሳምረን የተዝካር ድግስ ለመብላት ከመሄድ ይልቅ፥ በእንዲህ አይነቱ የመታሳቢያ ቦታ መገኘት ክርስቶስን ያስደስተዋል:: ሰሎሞንም "ለሁሉም ጊዜ አለው"ያለውን ሳይረሳ "ወደዘፈን ከመሄድ ወደልቅሶ ቤት መሄድ" ይሻላል ማለቱ ይህንን የመሰለውን መታሰቢያ አጉልቶ ለማሳየት ነው:: ቅዱስ ጳውሎስም ለእርሱ ስለሆኑት ይልቁንም ስለ ቤተሰቦቹ የማያስብ ማንም ቢሆን ሃይማኖት የካደ ከማያምን ሰው ይልቅ የከፋ ነው"(፩ኛ ጢሞ ፭:፰) እንዳለው፥ ይህን ጥሪ ተቀብሎ በሚደረገው መታሰቢያ አለመተባበር እራስን ከሰባዊ ውጭ ብቻ አይደለም ከሃይማኖትም ውጭ ማድረግ ነው::

የኢትዮጵያ ሕዝብ ሆይ! ከዚህ በፊት ማስገደል ቀርቶ ማሳሰር በማያስችሉ ምክንያቶች ከቤታቸው፥ ከትምህርት ቤታቸው፥ ከሕዝቡ ጉያ እየተመዘዙ የተገደሉትም፥ የታሠሩትም፥ የደረሱበት ያልታወቁትም፥ በስደት ዓለም መከራ የሚያዩትም፥ ባገር ውስጥም ጆሯቸው እንዳይሰማ ዐይናቸው እንዳያይ አንደበታቸው እንዳይናገር የታፈኑትንም ለማስታወስ፥ ወደፊትም ይህን መሳይ አሰቃቂ ግፍና በደል እንዳይደገም፥ የነፍሰ ገዳዮችን ጭካኔ፥ የሞቱትን ቆራጥነትና ታማኝነትን ለሰሚው ሁሉ በመመስከር መታሰቢያቸውን እናስታውስ:: እግዚአብሔር የሞቱትን ንፍስ ይማርልን:: ቤተሰባቸውንም ያጽናናልን:: በሕይወት ያለን እኛም በኅብረት በመንፈስ በርትተን ለቤተ ክርስቲያናችን ለጠቅላላው ወገናችን ቋሚ ሥራ ሠርተን ለማለፍ ያብቃን::

መድኃኔዓለም በቀራንዮ መስቀል ላያ ባፈሰሰው ደሙ፥ ኢትዮጵያን አጥቦ እንዲቀድሳት የዘወትር ጸሎታች ይሁን::

ለይኩን! ለይኩን! አሜን::

*ለሌሎች የቂሲስ አስተራየ ጽጌ ጦማሮች የሚከተለውን ድህረ-ገጽ ይመልከቱ፥*
***http://www.medhanialemeotcks.org/***